# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ



## የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ እና እድሣት ዳይሬክቶሬት

**በተሻሻለው የመምህራንና የት/ቤት አመራሮች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ እና እድሣት አፈጻጸም መመሪያ ዙሪያ ለክ/ከተማ የሙያ ፈቃድ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም ለከተማ አስተዳደሩ መምህራን ማህበር ተወካዮች የቀረበ የአሰልጣኞች ስልጠና**

ጥቅምት 2010 ዓ.ም

# የሙያ ፈቃድ ምንድነው?



- የሙያ ፈቃድ ማለት ፡-መምህራን የትም/አመራሮችና ሌሎችም ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀው ሥነ ምግባር፣ እውቀት፣ ክህሎትና የተግባራት ክንውንን ባካተተ ሁኔታ የተቀመጠውን የሙያ ብቃት ደረጃ (Professional Competence Standard) ማሟላታቸውን በማረጋገጥ በሙያው እንዲሰሩ የሚያስችል በሕግ በተፈቀደለት ካውንስል ወይም መ/ቤት የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

## የመምህራንና የት/ቤት አመራሮች ሙያፈቃድ ፋይዳ

- ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት በሀገሪቱ እንዲኖር ያግዛል፣
- በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የተሻለ አቅም ያላቸውንና በሥነ-ምግባር በሚገባ የታነፁ ባለሙያዎችን ወደ ሙያው ለመሳብና በሙያው እንዲቆዩ ያስችላል፣
- በሙያው ላይ ያሉ ነባር መምህራን ብቃታቸውን እያሳደጉ ይበልጥ ተወዳዳሪ እየሆኑ ሙያውን ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ይረዳል፣
- መምህራንና የትምህርት ተቋማት አመራር በሚያስመዘግቡት ውጤት ልክ ዕውቅናና ማበረታቻ እንዲያገኙ ይረዳል፣
- ውጤታማ የሆኑ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በሥራቸው እንዲተጉና ለበለጠ ውጤት እንዲነሳሱ ያደርጋል፣

# የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ እና እድሣት አፈጻጸም መመሪያ ዓላማ



- የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት የመምህራን፣ የርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮችን ሙያዊ የብቃት ምዘና ሂደትን በወጥነት ለመተግበርና
- በሙያ ፈቃድ አሰጣጥ የአደረጃጀቶችን ሚናና የፈጻሚ ባለድርሻ አካላትን ተግባርና ሃላፊነት ለይቶ ለማሳወቅና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መፍጠር ነው፡፡

# የተፈጻሚነት ወሰን

- ከቅድመመደበኛ እስከ መሰናዶ ባሉ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በሚሠሩ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች፣
- ከቅድመመደበኛ እስከ መሰናዶ ባሉ የግል ትምህርት ቤቶች በሚሠሩ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች፣
- ከቅድመመደበኛ እስከ መሰናዶ ባሉ የሃይማኖት ተቋማት ሥር በሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች በሚሠሩ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች፣
- ከቅድመመደበኛ እስከ መሰናዶ ባሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሥር በሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች በሚሠሩ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች፣
- በመንግሥትና በግል የመምህራን አሠልጣኝ ተቋማት በሚሠሩ መምህራን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# የሙያ ፈቃድ ዓይነቶች

- በሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ውስጥ ሶስት የሙያ ፈቃድ ዓይነቶች ይኖራሉ



ሀ) የመጀመሪያ የሙያ ፈቃድ (INITIAL PROFESSIONAL LICENSE)

ለ) ሙሉ የሙያ ፈቃድ (FULL PROFESSIONAL LICENSE)

ሐ) ቋሚ የሙያ ፈቃድ (PERMANENT PROFESSIONAL LICENSE) ናቸው።

## ሀ) የመጀመሪያ ሙያ ፈቃድ



- **የመጀመሪያ የሙያ ፈቃድ** ፦ለመምህራንና ለትምህርት ቤት አመራሮች ለሁለት ዓመት ብቻ የሚያገለግል ሆኖ የመምህርነት ስልጠና ለወሰዱና ከመምህራን ትምህርት ተቋማት በመምህርነት ወይም በትምህርት ተቋማት አመራርነት ሰልጥነው ወደሙያው ለሚገቡና ለደረጃው የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ለሟሉ ሙያተኞች የሚሰጥ የሙያ ፈቃድ ዓይነት ነው።

## ለ) ሙሉ የሙያ ፈቃድ

**ሙሉ የሙያ ፈቃድ**፦የመጀመሪያ ሙያ ፈቃድ በመያዝ ሲሠሩ ቆይተው ያጠናቀቁ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ፈቃዱን ለማግኘት ለደረጃው የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ላሟሉ ሙያተኞች የሚሰጥ የሙያ ፈቃድ ነው። ሙሉ የሙያ ፈቃድ **ለአምስት ዓመት** ያገለግላል ።

## ሐ) ቋሚ የሙያ ፈቃድ

**ቋሚ የሙያ ፈቃድ**፦ሙሉ የሙያ ፈቃድ ይዘው በዚህ ደረጃ የሚደረጉትን የሙያ ፈቃድ አገልግሎት አጠናቀው ፈቃድ ለማግኘት ለደረጃው የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ላሟሉ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሚሰጥ ፈቃድ ነው። ቋሚ የሙያ ፈቃድ የመጨረሻው የሙያ ፈቃድ ደረጃ ይሆናል።


የመምህራን ሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ስርአት ስዕላዊ መግለጫ
የሙያ ብቃት ደረጃ
የሙያ ፈቃድ አይነት
የቆይታ ጊዜ
ግራጁዌት
የመጀመሪያ ሙያፈቃድ
2 ዓመት
ፕሮፌሽንት
ሙሉ የሙያ ፈቃድ
5 ዓመት
አኮምፕሊሽ
ድ
ቋሚ ሙያ ፈቃድ
5 ዓመት
ሊድ
በየአምስት ዓመት ዕድሣት

# የርዕሰ መምህራን ና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ስርአት ስዕላዊ መግለጫ



# የሙያ ፈቃድ እድሳት



- በትምህርት ቤትና በመምህራን ትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ቋሚ የሙያ ፈቃድ ከያዙ በኋላ **በየአምስት አመት** የሙያ ፈቃዳቸውን ያድሳሉ፡፡

# የመምህራን ትምህርት ተቋማት መምህራን የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አፈጻጸም



## የመጀመሪያ ሙያ ፈቃድ

የመጀመሪያ ሙያ ፈቃድ ህጋዊ እውቅና ካለው ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ቢያንስ በባችለር ዲግሪ ደረጃ በመመረቅ በረዳት ምሩቅነት ደረጃ I እና II ያገለገለ ወይም የማስተርስ ዲግሪ ደረጃ በመያዝ በረዳት ሌክቸረርነት የተቀጠሩ ሆነው በየደረጃው የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ለሚሉ አሠልጣኝ መምህራን የሚሰጥ ሆኖ ለሁለት ዓመት ያገለግላል።

# ሙሉ የሙያ ፈቃድ



ሙሉ የሙያ ፈቃድ የመጀመሪያ ሙያ ፈቃድ በመያዝ ሲሠሩ ቆይተው የጠናቀቁ ወይም የማስተርስ ወይም የዶክቶሬት ዲግሪ ይዘው የመምህራን አሠልጣኝነት ሙያዊ ሥልጠና ወስደው ለጠናቀቁ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን ፈቃድን ለማግኘት ለደረጃው የሚሰጠውን መመዘኛ ሲያሟሉ የሚሰጥ ሆኖ ፈቃድ ለአምስት ዓመት ያገለግላል።

# ቋሚ የሙያ ፈቃድ

ቋሚ ሙያ ፈቃድ ሙሉ የሙያ ፈቃድ ላላቸውና ፈቃዱን ለማግኘት አሠልጣኝ መምህራን ለደረጃው የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ሲያሟሉ የሚሰጥ የሙያ ፈቃድ ነው፡፡ ቋሚ የሙያ ፈቃድ የመጨረሻ የሙያ ፈቃድ ነው።



- የሙያ ፈቃድ እድሳት፡-

በትምህርት ቤትና በመምህራን ትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ቋሚ የሙያ ፈቃድ ከያዙ በኋላ በየአምስት አመት የሙያ ፈቃዳቸውን ያድሳሉ፡፡

# የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና

- የጽሑፍና የማህደረ-ተግባር ምዘናዎች



የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮችን

ሙያዊ ብቃት ማረጋገጫ ሆነው ያገለግላሉ ።

# ለምዘና መሣሪያዎቹ የተሰጠ ክብደት

**ሀ/ ለጽሁፍ ምዘና (WRITTEN TEST) 80%**



**ለ/ ለማህደረ-ተግባር ምዘና (PORTFOLIO) 20%**

## የተመዛኞች ማለፊያ ነጥብ



- ማንኛውም በመምህርነት፣ርዕሰ-መምህርነትና ሱፐርቫይዘርነት ሙያ ሲሰሩ የቆየ ተመዛኝ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በጽሑፍና በማህደረ-ተግባር ምዘና ድምር ውጤት 70% ማምጣት ይጠበቅበታል።
- ከመምህራን ትምህርት ተቋማት ተመርቀው ወደ ሙያው ለሚገቡ አዲስ መምህራን የሚሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ሙሉ በሙሉ በጽሁፍ ምዘና ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከ100% ይወሰዳል፡፡

## የቀጠለ...

- ለብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው የጽሑፍ ምዘና ለነባር ተመዛኝ በሰለጠነበት የትምህርት አይነትና ትምህርቱ በሚሰጥበት ቋንቋ ሲሆን አዲስ ተመራቂ ተመዛኝ በሰለጠነበት እርከንና ቋንቋ ይሰጣል።
- የተመዛኞች ማህደረ-ተግባር ምዘና ተመዛኞቹ በሚገኙበት ተቋም ወይም ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ ተቋም ውስጥ ይካሄዳል።
- የብቃት ማረጋገጫ ምዘና መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አፈጻጸም በምዘና ማዕቀፎችና በምዘና አስተዳደር መመሪያ መሰረት ይሆናል

## የዳግም ምዘና አፈጻጸም

- ምዘና ወስደው የሚፈለገውን ውጤት ያላገኙ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በያዙት የሙያ ፈቃድ እየሠሩ ያለባቸውን ክፍተት በመለየትና እራሳቸውን በማብቃት በቀጣዩ ዓመት በድጋሚ እንዲመዘኑ ይደረጋል።
- ለሁለተኛ ጊዜ በተሰጠው እድል ተመዝነው የሚጠበቀውን ውጤት ካላገኙ ለሶስተኛ ጊዜ በቀጣዩ ዓመት እንዲመዘኑ ይደረጋል።
- ለሶስተኛ ጊዜ በተሰጠው ምዘና ማለፍ ካልቻሉ በያዙት ሙያ መቀጠል ስለማይችሉ በሲቪል ሰርቪስ የሰራተኛ መተዳደሪያ አዋጅ መሰረት ውሳኔ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

## ለቀጣይ ደረጃ ሙያ ፈቃድ ስለማመልከት

- ለየሙያ ደረጃው የቆይታ ጊዜ ከማጠናቀቃቸው አንድ አመት በፊት ለሚገኙበት ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው።



- የሙያ ፈቃድ ለማደስ ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-
  - የሙያ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ፣
  - የሙያ ፈቃድ ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ ለ5 ዓመታት በመምህርነት ወይም በት/ቤት አመራርነት ሥራ ላይ የቆዩበት ማስረጃ ማቅረብ፣
  - በሙያ ፈቃድ እድሳት ምዘና ተፈላጊውን ውጤት ማስመዝገብ፣
  - የመልካም ሥነ-ምግባር ማስረጃ፣

# የሙያ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

- በምዘናው የሚጠበቀውን ውጤት ያስመዘገቡ መምህራን፣ርዕሳነ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡



- የምስክር ወረቀቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጅ ሆኖ አስፈላጊ መረጃዎች የያዘ ይሆናል፡፡

- በተለያዩ ምክንያት ከመምህርነት ወይም ከርዕሰ መምህርነት ወይም ከሱፐርቫይዘርነት ሙያ የሚሰናበቱ ባለሙያዎች ተሰጥቷቸው የነበረው የሙያ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡
- የሙያ ፈቃድ የሚሠረዝባቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች ፡-
    - የሙያ ፈቃድ ከተገኘበት የሥራ ዘርፍ መልቀቅ
    - የሥነ ምግባር ጉድለት፣
    - በብቃት ማነስ የተሰናበተ

## የምዘና አፈጻጸም

ሀ/ የምዘና ዝግጅት በስታንዳርዱ መሰረት ለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚዘጋጁ የምዘና መሳሪያዎች በፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ይዘጋጃሉ፡፡



ለ/ መዛኞችን በተመለከተ፡-የጽሁፍ መዛኞች በተዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት መሰረት ከትምህርት ተቋማት፣ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከክልል ት/ቢሮ ባለሙያዎች ይመረጣሉ፡፡

- የማህደረ-ተግባር መዛኞች በሙያቸውና በስነምግባራቸው የተመረጡ፣ በማህደረ-ተግባር ምዘናና ውጤት አሰጣጥ ላይ በቂ ግንዛቤና ልምድ ያላቸው የትምህርት ባለሙያዎች ይሆናሉ፡፡

# መብቶችና ግዴታዎች

## መብቶች

ሀ/ የሙያ ፈቃድ ያላቸው መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የትምህርት ተቋማትና የትምህርት እርከኖች የመስራት መብት አላቸው።



ለ/ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የያዙት የሙያ ፈቃድ የቆይታ ጊዜው ሲያበቃ ባሉበት ክልል ለሚቀጥለው ደረጃ ሙያ ፈቃድ የማመልከትና የመመዘን መብት አላቸው።

ሐ/ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

መ/ መምህራን፣ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ስለሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አሰራር የማወቅና በቂ ግንዛቤ የመያዝ መብት አላቸው።

ሠ/ በሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያላቸው ባለሙያዎች በየደረጃው ለሚመለከታቸው የቅሬታ ሰሚ አካላት ቅሬታቸውን የማቅረብና ተገቢውን ውሳኔ ከበቂ መረጃ ጋር በወቅቱ የማግኘት መብት አላቸው።

ሀ) ማንኛውም መምህር ወይም ርዕሰ መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር በሙያው ለመቀጠል የሙያ ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል።

ለ) ማንኛውም መምህር ወይም ርዕሰ መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር የሙያ ፈቃድ ለማሻሻል ቀድሞ በያዘው የሙያ ፈቃድ መሥራቱን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚሰራበት ተቋም ማቅረብ ይጠበቅበታል።



ሐ) ማንኛውም መምህር ወይም ርዕሰ መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር በስራው ለመቀጠል ህጋዊ የሙያ ፈቃድ ይዞ መገኘት ይገባዋል።

መ) በሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ለሚደረጉ የሥራ እንቅስቃሴዎች ስኬት የትምህርት ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለሥራው የሚፈለገውንና የሚጠየቀውን መረጃ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

# በሙያ ፈቃድ አሰጣጥ የፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት

ሀ) በፌዴራል ደረጃ

- የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አጠቃላይ ሂደትና አተገባበሩን በበላይነት የሚያስተባብር አገር አቀፍ ካውንስል ይቋቋማል። 32 አባላት ይኖሩታል ተጠሪነቱም ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።
- የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አተገባበርን በትምህርት ሚኒስቴር አጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ስር የተደራጀው የመምህራንና ትምህርት ቤት አመራሮች ሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ዳይሬክቶሬት ስራውን በባለቤትነት ይመራል።

# የካውንስል አባላት፦

1. የአጠቃላይ ትምህርት ሚኒስትር ደኤታ (ሰብሳቢ)
2. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፕሬዘዳንት (ም/ሰብሳቢ)



3. የመምህራንና የት/ቤት አመራሮች ሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር (ፀሐፊ)
4. የመምህራንና የትምህርት አመራር ሌማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር (አባል) 5. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ተወካይ (አባል) (2)

6. ከክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃሊፊዎች (አባል) (11)

7. ከመም/አመ/አሰሌጣኝከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጋራ መድረክ (አባል) (7)

8. የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተወካዮች (አባል) (4)

9 .ከግሌ የትምህርት ተቋማት ማኅበር (አባል) (1)

10 .ከኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ፌደሬሽን (አባል) (1)

11. ከሴቶች ማህበር (አባል) (1)

12. ከወጣቶች ማህበር (አባል) (1)



- ካውንስለ በዓመት አንዴ ጊዜ በመሰብሰብ ተግባራቱን ያከናውናሉ።ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰበሰብ ይችላል ፡፡
- የካውንስለ አባላት ስብጥርም ወቅታዊ አደረጃጀትን ግምት ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡

## ለ) በክሌሌ/በከተማ አስተዳደርር ደረጃ

- የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን በክልል ደረጃ በበላይነት የሚመራ ካውንስል በክልል ትምህርት ቢሮ ሃላፊ ወይም በሚወከል ሰብሳቢ የሚመራ ሲሆን በክልል ደረጃ ሥርዓቱን ለመምራት፣ ለማስተዳደርና ለመተግበር የተቋቋመውን የሙያ ፈቃድ ዘርፍ የሚመራ ሃላፊ በፀሐፊነት ያገለግላል።
- የክሌሌ/የከተማ አስተዳደር ካውንስል የየክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ያደረገ ከፌደራል ካውንስል አወቃቀር ጋር ተመሳሳይነት ያለው አደረጃጀት ይኖረዋል።

# የፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ሃላፊነት

## በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋመው ካውንስል ተግባርና ሃላፊነት



ሀ) የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አፈጻጸሞችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል።

ለ) የመምህራን፣የርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የአፈፃፀም መመሪያዎችን ደንቦችና ስታንዳርዶችን በመገምገም ያፀድቃል።

ሐ) የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ያጋጠሙ የአፈፃፀም ችግሮችን ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሰጣል።

- የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አፈጻጸም መመሪያዎችን ማንዋሎችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል።
- የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ምዘና መሳሪያዎችን ያዘጋጃል።
- የሁለተኛ ደረጃ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ምዘና ያሳትማል፣ ያሰራጫል፣ ምዘና ያካሂዳል።
- የሁለተኛ ደረጃ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ምዘና ውጤት ትንተና ያካሂዳል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል።

# በክሌሌ ደረጃ የካውንስለ ተግባርና ሃላፊነት

**ሀ)** ከትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅተው ለትግበራ የሚላኩ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርድች ከክልል ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው በትክክል መተግበራቸውን ያረጋግጣል።

**ለ)** የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓትን ይገመግማሌ፣ የማስተካከያ ሃሳቦችን ይሰጣሉ።

ሐ) የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ያጋጠሙ የአፃፀም ችግሮችን ይመረምራሉ፤ አጠቃላይ የመፍትሔ ሃሳብ ይሰጣ ሉ።

መ) በክልል ደረጃ የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት አፈጻጸምን ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፣ ግብረመልስ ይሰጣሉ ።

ሠ) በክልል የሚሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ የጽሑፍና የማህደረ-ተግባር ምዘና ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ያስዳድራሉ ።

## ክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፡-

- በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ የተዘጋጁትን የሙያ ብቃት ምዘናዎች ያስተዳድራሉ።
- የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ምዘና ውጤት ትንተና ያካሂዳሉ፣ ግብረ መልስ ይሰጣሉ።



- የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ትግበራን በመከታተል ስታትስቲካዊ መረጃዎችን በማጠናከር በየወቅቱ ለፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል።
- ለዞኖችና ለወረዳዎች ሥልጠናዎችንና የማቴሪያል ድጋፎችን በመስጠት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራሉ።

## የቅሬታ ሰሚ አካል ስለማቋቋምና ቅሬታ ስለማቅረብ

- የቅሬታ ሰሚ አካል ከክልል ጀምሮ በየደረጃው የሚደራጅ ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑም ሁለት ዓመት ይሆናል።
- በየደረጃው የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከአምስት ያልበለጡ አባላት ስብጥር ይዞ ይደራጃል። በዚህ መሠረት፦



ሀ/ በክልል/በከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ደረጃ አንድ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፤ ተጠሪነቱ ለክልል/ለከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ይሆናል።

ለ/ በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ አንድ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፤ ተጠሪነቱ ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል።

## የቅሬታ አቀራረብ

ሀ/ በሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ቅሬታ ያለው አመልካች ቅሬታ በቀረበበት ጉዳይ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል።



ለ/ ውሣኔ ሰጪው ወገን ለቅሬታ አቅራቢው ቅሬታው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

ሐ/ ቅሬታ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (ለ) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ባያገኝ ወይም የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ ሳያገኘው ቢቀር ጉዳዩን ወደ ቀጣዩ ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡በክልል ደረጃ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ቅሬታ ይቀርብባቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ጉዳዮች

- የጽሁፍና የማህደረ ተግባር ምዘናዎች በትክክል አለማረም፣
- የምዘና ውጤት በትክክል አለመመዝገብ፣
- ከምዘና መታገድ ወይም መከልከል፣
- የሙያ ፈቃድ የምስክር ወረቀት መከልከል ወይም መሰረዝና፣
- ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ።

- የሙያ ፈቃድ ሥርዓት ከመዘርጋቱ በፊት በተለያየ ሙያዊ የእድገት መሰላል (ደረጃ) ላይ ያሉ ነባር መምህራን፣ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ወደ ሥርዓቱ ለማስገባት እንዲቻል አሁን በሚገኙበት የእድገት ደረጃ ትይዩ ተመዝነው ለደረጃው የሙያ ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

# ነባር መምህራን

ሀ) በመለስተኛ የደረጃ ዕድገት መሰላል ላይ ያሉ መምህራን ለመጀመሪያ የሙያ ፈቃድ ይመዘናሉ፣

ለ) በመምህርና በከፍተኛ መምህር የደረጃ ዕድገት መሰላል ላይ ያሉ መምህራን ለሙሉ የሙያ ፈቃድ ይመዘናሉ፣



ሐ) በተባባሪ መሪ፣ በመሪና በከፍተኛ መሪ መምህር የደረጃ ዕድገት መሰላል ላይ ያሉ መምህራን ለቋሚ የሙያ ፈቃድ ይመዘናሉ፣

መ) እድሚያቸው 55 ዓመት እና በላይ የሆናቸው ነባር መምህራን ለሙያ ፈቃድ ምዘና ጥያቄ ካላቀረቡ በስተቀር ለመመዘን አይገደዱም፡፡

# ነባር ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች

ሀ) በጀማሪ ርዕሰ መምህር ወይም በተባባሪ ሱፐርቫይዘር ደረጃ ላይ ያሉ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለመጀመሪያ የሙያ ፈቃድ ይመዘናሉ፣



ለ) በርዕሰ መምህር ወይም በሱፐርቫይዘር ደረጃ ላይ ያሉ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለሙሉ የሙያ ፈቃድ ይመዘናሉ፣

ሐ) በከፍተኛና በመሪ ርዕሰ መምህርና ሱፐርቫይዘር ደረጃ ላይ ያሉ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለቋሚ የሙያ ፈቃድ ይመዘናሉ፣

መ) እድሜያቸው 55 ዓመት እና በላይ የሆናቸው ነባር የት/ቤት አመራሮች ለሙያ ፈቃድ ምዘና ጥያቄ ካላቀረቡ በስተቀር ለመመዘን አይገደዱም፡፡

## ጊዜያዊ ፈቃድ

- ጊዜያዊ ፈቃድ በአስገዳጅ ሁኔታዎች በመምህርነት ወይም በርዕሰ መምህርነትና በሱፐርቫይዘርነት ሙያዊ ሥልጠና ሳይወስዱ በማስተማር ወይም በአመራር ሥራ እንዲያገለግሉ ከቅድመ መደበኛ እስከ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ለተመደቡ ወይም በብቃት ምዘና የማለፊያ ውጤት ላላመጡ ነባር መምህራን፣ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች እንደየሁኔታው ከሁለት እስከ ሶስት ዓመታት ብቻ እንዲያገለግል በጊዜያዊነት የሚሰጥ ፈቃድ ነው። ጊዜያዊ ፈቃድ አይታደስም።

# የቀጠለ...



## ለመጀመሪያ ደረጃ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች

- በትምህርት ዝግጅቱ/ቷ ቢያንስ 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች፣
- የመጀመሪያ ደረጃ መምህርነት የትውውቅ ሥልጠና ያገኘ/ች፣
- በሙያው ለመሥራት ዝንባሌ ያለው/ያላት፣
- በሂደት የሙሉ መምህርነት ሥልጠና ለመውሰድ ግዴታ የሚገባ/የምትገባ፣

## ለሁለተኛ ደረጃ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች

- በትምህርት ዝግጅቱ/ቷ ቢያንስ ለደረጃው የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት ያለው/ያላት፣
- የሁለተኛ ደረጃ መምህርነት የትውውቅ ሥልጠና ያገኘ/ች፣
- በሙያው ለመሥራት ዝንባሌ ያለው/ያላት፣
- በሂደት የሙሉ መምህርነት ሥልጠና ለመውሰድ ግዴታ የሚገባ/ የምትገባ፣

## ተጠያቂነት

- በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ ባለሙያዎችና ሃላፊዎች በሙያ ፈቃድ አተገባበር ዙሪያ ለሚፈጽሟቸው ጥፋቶች በሕግ አግባብ ተጠያቂ ይሆናሉ።

## የሽግግር ጊዜ ድንጋጌ

- ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት በመምህርነትና በትምህርት ቤት አመራርነት የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ባለሙያዎች ከጹሁፍ ምዘናው የሚጠበቀውን ውጤት ያስመዘገቡ ከሆነ ፈቃድ ሰጪው አካል በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማህደረ-ተግባር ምዘና በማካሄድ ምዘናውን ያለፉ የሙያ ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህንን መፈጸም ካልተቻለ በዚህ መመሪያ ክፍል 2 ቁጥር 4.8 የተጠቀሰው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# አመሰግናለሁ